## ኢትዮጵያ እና ደቡብ ሱዳን የተፈራረሙትን የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 983/2016 ላይ የቀረበ መግለጫ

### 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ እና ደቡብ ሱዳን በሚዋሰኑባቸው የጋራ ድንበር አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን በጠረፍ ንግድ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል በሁለቱ ሀገራት መካከል እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ 24 ቀን 2017 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ተፈርሟል። የዚህ የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል ዋና ዓላማ በሁለቱ ሀገራት የጋራ ድንበር አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ከመሀል ሀገር በቀላሉ ማግኘት የማይችሏቸውን መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች በህጋዊ የጠረፍ ንግድ አሰራር እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

በፕሮቶኮሉ አንቀጽ 4 ላይ ተፈራራሚ ሀገራቱ የጠረፍ ንግድ ማስፈጸሚያ መመሪያ በማውጣት ፕሮቶኮሉን መተግበር እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱም ሀገራት በኩል የማስፈጸሚያ መመሪያ ባለመውጣቱ ፕሮቶኮሉን እስካሁን መተግበር ሳይቻል ቆይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በሀገራችን በኩል ከደቡብ ሱዳን ጋር የሚዋሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች አንዳንድ መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶችን በመደበኛ ንግድ በቀላሉ ማግኘትና መጠቀም ያልቻሉ መሆኑን በመግለጽ ቀደም ሲል የተፈረመው የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል ወደ ትግበራ እንዲገባና መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች በጠረፍ ንግድ እንዲሟሉላቸው በተለያዩ ጊዜያት ጥያቄዎችን ሲያቀርቡ ቆይተዋል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በዚህ ዓመት በእቅድ ከያዛቸው ተግባራት መካከል ከደቡብ ሱዳን ጋር የተፈረመውን የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል ወደ ትግበራ ለማስገባት የሚያስችል የጠረፍ ንግድ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግና የድንበር አካባቢ ማህበረሰቦችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚለው ይገኝበታል፡፡ ስለሆነም ሀገራችን ከደቡብ ሱዳን ጋር የተፈራረመችውን የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል ለማስፈጸም የሚኒስቴር መ/ቤቱ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 35 (2) እና 52(2) በተሰጠው

ስልጣን መሰረት በኢትዮጵያ እና በደቡብ ሱዳን የድንበር አካባቢዎች ተፈጻሚ የሚሆን የጠረፍ ንግድ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

## 2. የመመሪያው አጠቃላይ ይዘት

ረቂቅ መመሪያው በአጠቃላይ በሦስት ክፍሎች እና በ12 አንቀጾች የተደራጀ ሲሆን የወጪ እና የገቢ ምርቶችን የሚዘረዝሩ ሁለት አባሪዎችም አሉት፡፡

በመመሪያው የተካተቱ ድንጋጌዎች ከሀገራችን የንግድ ህጎች፣ ደንቦች እና አሰራሮች ጋር የተጣጣሙ ሲሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮችም፡-

- የመመሪያው አጭር ርዕስ እና የቁልፍ ቃላት ትርጓሜዎች፣
- በጠረፍ ንግድ ስራ ላይ መሰማራት ስለሚችሉ ሰዎች እና በጠረፍ ንግድ ስለሚነገዱ ምርቶች፣
- የወጪና የገቢ ምርቶች ዋጋ አተማመን፣
- በጉምሩክ በሮች ለጠረፍ ነጋዴዎች ስለሚሰጡ አገልግሎቶች፣
- የመረጃ ልውውጥ፣
- የጠረፍ ንግድ ፈቃድ አጠቃቀም እና
- ሌሎች ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

የመመሪያው ሁለት አባሪዎች የጠረፍ ንግድ የሚካሄድባቸውን የወጪና ገቢ ምርቶች ዝርዝር የያዙ ናቸው፡፡ አባሪ-1 ከሀገራችን ወደ ደቡብ ሱዳን የሚወጡ ምርቶችን የሚያሳይ ሲሆን አባሪ-2 ደግሞ ከደቡብ ሱዳን ወደ ሀገራችን የሚገቡ ምርቶችን ይዘረዝራል፡፡

## 3. የመመሪያው አስፈላጊነት

የጠረፍ ንግድ መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ሀገራችን ከደቡብ ሱዳን ጋር የተፈራረመችውን የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል በሀገራችን የንግድ አሰራር ስርዓት መሰረት ወደ ትግበራ በማስገባት በሀገራችን በኩል ከደቡብ ሱዳን ጋር የሚዋሰኑ የድንበር አካባቢ ማህበረሰቦች ከመሀል የሀገራችን ክፍሎች በቀላሉ ማግኘት የማይችሏቸውን የፍጆታ ምርቶች በጠረፍ ንግድ እንዲቀርቡላቸው ለማድረግ ነው፡፡

በተጨማሪም በድንበር አካባቢ ህጋዊ የጠረፍ ንግድ አሰራርን መተግበር በአካባቢው የሚስተዋለውን የኮንትሮባንድ እና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ለመቀነስ፣ በኢትዮጵያ እና በደቡብ ሱዳን ጎረቤት ሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር በድንበር አካባቢ ሰላምና ፀጥታ ለማስፈን እና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር የጠረፍ ንግድ መረጃ አያያዝንና ቁጥጥርን ለማጠናከር የላቀ ፋይዳ እንደሚኖረው ታምኖበታል፡፡

## 4. በረቂቅ መመሪያው ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች

ረቂቅ መመሪያው ይመለከተናል የሚሉ አካላት ሁሉ አስተያየት እንዲሰጡበት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቴሌግራም ድረ-ገጽ ከሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የተለቀቀ ሲሆን በድረ-ገጹ የተለቀቀ ስለመሆኑም በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች መረጃ ተላልፏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል የመንግስት ተቋማት እንደዚሁም የግሉ ዘርፍ ተወካዮች ያላቸውን አስተያየት የሰጡበት መድረክ በአዳማ ከተማ ተዘጋጅቶ የነበረ ሲሆን በመድረኩ ከጉምሩክ ኮሚሽን፣ ኢሚግሬሽንና የዜግነት አገልግሎት፤ በጋምቤላ ክልል ከክልሉ ንግድ ቢሮ፣ ከፓጋጊ ንግድ ጽ/ቤት እና ከፓጋጊ ወረዳ የነዋሪዎች እና የድንበር አካባቢ ነጋዴዎች ተወካዮች፤ በአፋር ክልል ከክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ፣ ከኤልዳሀር ወረዳ ንግድ ጽ/ቤት እና የኤልዳሃር ወረዳ ነዋሪዎች እና የድንበር አካባቢ ነጋዴዎች ተወካዮች፤ በሶማሌ ክልል ከክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ፣ ከአይሻ ወረዳ ንግድ ጽ/ቤት እና የአይሻ ወረዳ ነዋሪዎች እና የድንበር አካባቢ ነጋዴዎች ተወካዮች፤ እንዲሁም ከሚኒስቴር መ/ቤታችን የተለያዩ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ተወካዮች ተሳትፈዋል፡፡

በውይይት መድረኩ ከባለድርሻ አካላት የተነሱ አግባብነት ያላቸው አስተያየቶች በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡ በተለይም የጠረፍ ንግዱ የሚካሄድበት የጋምቤላ ክልል ተወካዮች በዋናነት ያነሱት አስተያየት ቀደም ሲል በረቂቁ የተካተተው የንግዱ የገንዘብ መጠን ብር 20,000 ብቻ መሆኑ በንግዱ የሚሠማሩትንም ሆነ በጠረፍ ንግዱ ተጠቃሚ የሚሆኑትን የክልሉን ነዋሪዎች በሚፈለገው መጠን ተጠቃሚ ለማድረግ ስለማያስችል የገንዘብ መጠኑ ከፍ እንዲል የሚል በመሆኑ በዚሁ አስተያየት መሠረት የንግዱ

የገንዘብ መጠን ወደ 40,000 ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ ይህን እና ሌሎች አስተያየቶችን ተቀብሎ በማካተት ረቂቅ መመሪያው እንዲጻብር ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

በመጨረሻም ረቂቅ መመሪያው ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም በቁጥር 01.1.14.4/50270 በተጻፈ ደብዳቤ ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኮ ህዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም በቁጥር ፍሚ05/6078 10.1 በተጻፈ ሽኚ ደብዳቤ አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን የፕሮቶኮሉን መጽደቅ ከሚመለከተው በስተቀር የተሰጡ ሁሉም አስተያየቶች ተወስደው አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

መመሪያው ለማስፈጸም ዓላማ ያደረገው የኢትዮጵያ እና ደቡብ ሱዳን የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ማዋዋያና ማጽደቂያ ስነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1024/2009 እንዲሁም በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 9(4) እና 52(12) መሰረት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ያልጸደቀ በመሆኑ ከመመሪያው በፊት ፕሮቶኮሉን ማጸደቅ እንዲቀድም ወይም ያለ ፕሮቶኮሉ (ስምምነቱ) መመሪያ ማውጣት የሚቻልበት ሁኔታ እንዲታሰብ በሚል የተሰጠውን አስተያየት በተመለከተ ሀገራችን የምትፈራረማቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የድርድር፣ የመፈራረም እና የማጸደቅ ሂደት በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ማዋዋያና ማጽደቂያ ስነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1024/2009 መሰረት ህጋዊ ሂደትን መከተል እና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጽደቅ ያለባቸው መሆኑ ለሁሉም ግልጽ የሆነ ጉዳይ ቢሆንም በዚሁ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ማዋዋያና ማጽደቂያ ስነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1024/2009 አንቀጽ 18 በግልጽ እንደተመለከተው ሀገራችን ከሌሎች ሀገራት ጋር ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በትብብር ለመስራት፣ በዓለም አቀፍ ህግ የማይገዙና ህጋዊ ግዴታ የማያስከትሉ ሰነዶችን (Agreements) የዲፕሎማሲ መስመሩን በተከተለ መንገድ የምትፈራረማቸውን ሰነዶች ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አቅርቦ ማጸደቅ አያስፈልግም፡፡ በዚህም መሰረት ሀገራችን ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርበው ያልጸደቁ ግዴታ የማይጥሉ እና በዓለም አቀፍ ህጎች የማይገዙ በርካታ የመግባቢያ ሰነዶችንና የትብብር ስምምነቶችን የተፈራረመች ሲሆን ከእነዚህ ሰነዶች መካከል እ.ኤ.አ በ2017 ዓ.ም ከደቡብ ሱዳን ጋር የተፈረመው የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል አንዱ ነው፡፡

የሀገራችን እና የደቡብ ሱዳን መንግስታት የተፈራረሙት የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል በሁለቱ ሀገራት የድንበር አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎችን በየሀገራቱ ህጎች መሰረት በጠረፍ ንግድ ተጠቃሚ ለማድረግ በትብብር ከመስራት ባለፈ በሀገራችን ላይ ግዴታ የማያስከትል እና በዓለም አቀፍ ህግ የማይገዛ ነው፡፡ ፕሮቶኮሉ

ተግባራዊ የሚደረገውም ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ መሆኑ፣ ፕሮቶኮሉን በመተግበር ሂደት አለመግባባት ቢያጋጥም እንኳን አለመግባባቱ የሚፈታው የሁለቱ ሀገራት የጋራ የድንበር ንግድ ኮሚቴ በሚያደርገው ምክክርና ድርድር ብቻ መሆኑ እንዲሁም ፕሮቶኮሉን የሀገራችንም ሆነ የደቡብ ሱዳን መንግስት በማንኛውም ጊዜ ከ3 ወራት ቀደም ብሎ በሚገለጽ ደብዳቤ እንዲያበቃ/እንዲቋረጥ ማድረግ የሚችሉ መሆኑ በፕሮቶኮሉ አንቀጽ 9 እና 11 ላይ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ፕሮቶኮሉ በሀገራችን ላይ ግዴታ የማያስከትልና ለዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተገዢ አለመሆኑ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ታምኖበት የተፈረመ እና ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ መሆን የሚችል መሆኑ የተመለከተ በመሆኑ እንደሌሎች ስምምነቶች ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲጸድቅ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም፡፡

ሌሎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡ አስተያየቶች የተስተናገዱበትን ሁኔታ በተመለከተ ራሱን የቻለ ተጨማሪ ማብራሪያ ተዘጋጅቶ አባሪ ተደርጓል፡፡

ስለሆነም በዚህ ማብራሪያ ከዚህ በላይ በዝርዝር የቀረቡትን እና የሚኒስቴር መ/ቤታችሁ የሰጣቸው አስተያየቶች የተስተናገዱበትን ሁኔታ በተመለከተ በተዘጋጀው ተጨማሪ ማብራሪያ የቀረቡትን ሀሳቦች፣ አስተያየቶች እና የጋራ መግባባቶች ታሳቢ በማድረግ መመሪያው የጸደቀ በመሆኑ በአስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት እንዲመዘገብልን በአክብሮት አቅርበናል፡፡